የፖለቲካ ብዥታ ጠላትን አለማወቅ ብቻም ሳይሆን ዓላማንም ያስታል!ለውድቀትም ይዳርጋል!

ሚያዝያ22 ቀን 2015 ዓም(30-04-2023)

ዓላማና የሚጓዙበትን የትግል አቅጣጫን አለመረዳት፣ጠላትና ወዳጅንም አለማወቅ ለከፋ ውድቀት ይዳርጋል።ይህንን ተገንዝቦ አስፈላጊውን ሁሉ ጥንቃቄና ዝግጅት ያደረገ ትግል ምንም ያህል ውጣውረዱ ቢበዛ ግቡን እንደሚመታ ጥርጥር የለውም።የድሉን ጊዜ ሊያረዝመው ወይም ሊያሳጥረው ከሚችሉት ምክንያቶች አንዱና ዋናው በውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉትን ድክመቶች በጊዜው አለማሶገድና በጽናት አለመቆም፣ከአስመሳዮችና ከሰርጎገቦች ነጻ አለመሆን ነው።

ትግል ሲጀመር ማንንና ለምን እንደሚታገሉ፣በምንስ አይነት ትግል ካሰቡበት ግብ መድረስ እንደሚችሉ፣ የጠራ መመሪያ መያዝ፣ ሃይልና አጋራቸው ማን እንደሆነ መገንዘብ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው።በዚህ መሰናዶ ውስጥ የተሰለፈና ያለፈ ትግል የድል ባለቤት እንደሚሆን በብዙ ትግሎች ታሪክ የተመሰከረለት ሃቅ ነው።እርግጥ ነው በትግል ሂደት ውስጥ ይሆናል ብለው ያላሰቡትና ያልጠረጠሩት ሊከሰት ይችላል።ለዚያ ክስተት ደግሞ ዓላማን ሳይለቁና ሳይዘነጉ፣ለውጤት የሚያግዝ፣ከተከሰተው አደጋ ለመውጣት የሚረዳ ስልት በመቀዬስ ሁኔታና አቅም በፈቀደ ደረጃ ማስተካከልና እርማት ማድረግ ተገቢ ይሆናል።በትግል ወቅት በራስ ላይ መዝመት ፣ሂስና ግለሂስ ማድረግ ጤነኛ የፖለቲካ ህክምና ወይም መከላከያ መድሃኒት መጠቀም ማለት ነው።በዬጊዜው ይህ አሠራር መለመድና መወሰድ ይኖርበታል።ስለሂስና ግለሂስ ትልቁ የቻይናውያን አብዮት መሪ ማኦ ሴቱንግ ሲያስተምሩ ቤት በዬቀኑ ካልተጠረገ የቆሻሻ ክምር ይወርሰውና ለኗሪው ቤተሰብ የ ጤና ጠንቅ ይሆናል፣የፖለቲካ ድርጅትም እንዲሁ በሚሄድበት የትግል ጉዞ ውስጥ የታዩ ድክመቶቹን ወይም ጠንካራ ጎኖቹን ካልመረመረ ወይም ካልፈተሸ የመውደቂያ ምክንያቶቹን እዬገነባ ይሄዳል፣በመጨረሻም በጠላቶቹ ድል ይሆናል ብለዋል።በዚህ ህሳቤ የተገነባው የቻይናውያን አብዮታዊ ሃይል በውስጥ አገር ወዳዶቹን በማስተባበር የወራሪውን የጃፓንን ፋሽስታዊ ጦር ድል አድርጎ ለአሁኒቷ ቻይና የመሰረት ድንጋይ አስቀመጠ።እንግሊዝ አገራትን በመውረር፣በመዝረፍ፣በባርያ ንግድና በባርነት በታገቱ የሰው ልጆች እርካሽ ጉልበትና ላብ ጭምር በዘረጋችው የኢንዱስትሪ ምርት ውጤት ታግዛ ከአስር ትውልድ በላይ የፈጀባትን የእድገት ደረጃ ቻይና አገራትን ሳትወር፣በራሷ አቅምና ችሎታ በሁለት ትውልድ ውስጥ ብቻ መድረስ ሳይሆን አልፋ ከዓለማችን ሃያላን አገሮች ግንባር ቀደም ለመሆን በቃች።አሁንም የያዘችው የሶስተኛው ትውልድ ዘመን እቅዷም የዓለም አገራት ፊትአውራሪ ለማድረግ የሚያበቃት ነው።ይህንን ጉዞዋን ለማደናቀፍ አሜሪካኖችና አውሮፓውያን ያለ የሌለ ሃይላቸውን ተጠቅመው ግብግብ

ገጥመዋታል።የጦር ሜዳ ያደረጉትም የኤሽያና የአፍሪካ መሬት ነው።ነገሩ ከከረረ ለሶስተኛው ዓለም አውዳሚ ጦርነት ምክንያት ይሆናል ተብሎ ተፈርቶለታል።ይህንን አደጋ ለመቀልበስ የአፍሪካና የእስያ አገሮች የራሳቸውን ነጻነትና ልዑላዊነት ማስከበር ሲችሉና ከውጭ ሃይሎች ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት ፈትሸው ከባርነት ቀንበር ለመላቀቅ ተላላኪ የሆኑትን መሪዎቻቸውን ለማሶገድ የሚያስችል አህጉራዊ ግንባር ሲፈጥሩ ነው።ያ ካልሆነ እስከዛሬ ድረስ በዘላቂ ሰላም ያልተቋጨውና ለነገ ስጋት ተሸክሞ የሚጓዘው የትናንቱ የኢትዮጵያ፣ ዛሬ በሱዳን የተቀሰቀሰው የእርስበርስ ጦርነት ምህዳሩን አስፍቶ በሌሎቹም አገሮች የሚከሰት፣በሚሊዮን የሚቆጠር የሰው ልጅ ህይወት የሚቀጥፍና ከባቢን የሚያወድም የተልእኮ ጦርነት ይሆናል።ሳይቃጠል በቅጠል!

የመሪዎች የፖለቲካ ብስለት የሚለካው በነዚህ ወቅቶችና አጋጣሚዎች ኪሳራ ሳይገቡና ሳያጎበድዱ ትግሉ የሚሳካበትን መንገድና ብልሃት ማለትም ስልት በመቀዬስ ነው።በዚህ አይነቱ የፈተና ወቅት ደካማው ችግርና መከራ ሲበዛበት ከትግሉ ያፈነግጣል፤እጁን ይሰጣል።ጠንካራው ደግሞ የመጣውን ፈተና በጥንካሬ አልፎ ከድል ማማ ላይ ይዘልቃል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለብዙ ዓመታት ለክብሩና ለነጻነቱ ከውጭ ከመጣው ወራሪ ሃይል ጋር የሞት የሽረት ትግል ማድረጉና ያገሩን ነጻነት አስከብሮ መኖሩን የውጭ አገር ታሪክ ጸሃፊዎች ብቻም ሳይሆኑ ጠላቶቻችንም የመሰከሩት ሃቅ ነው።ባደረገው የሞት የሽረት ትግል የራሱም ወገን ከድቶት ከጠላት ጋር የተሰለፈ ባንዳ መኖሩም አይካድም።አርበኞቹን አሳልፎ የሰጠ፣ለጠላት የሰለለ፣ስንቅ ተሸክሞ መንገድ የመራም ብቻ ሳይሆን ነፍጥ አንግቦ የተዋጋ የኢትዮጵያ ልጅ ሆኖ እናት አገሩን የከዳ ብዙ ነው።በዚህ እኩይና የክህደት ተግባር ላይ የተሰለፉት የአንድ ጎሳ ተወላጆች ብቻ ሳይሆኑ ከሁሉም ጎሳ የተውጣጡ ነበሩ። በአርበኝነትም በዱር በገደል ሲፋለሙ የነበሩት እንዲሁ የአንድ ጎሳ ተወላጆች ብቻ ሳይሆኑ ከሁሉም ጎሳ የተውጣጡ አገር ወዳዶች ነበሩ።የአማራው አርበኛ እንዳለ ሁሉ የአማራ ባንዳ ነበር፣የትግራይ አርበኛ እንደነበር የትግራይ ባንዳም ነበር፣የኦሮሞ አርበኛ እንደነበረ ሁሉ የኦሮሞም ባንዳ ነበር፣ሌላውም እንዲሁ።በአርበኛነቱ የአማራው ቁጥር የበላይነቱን መያዙ አይካድም።በባንዳነቱም እንዲሁ የሰሜኑ ኢትዮጵያዊ ቁጥሩ ከፍተኛ ነበር።ለዚያም ምክንያቱ ለ40 ዓመታት በጣልያኖች ቅኝነት ተይዞ በመቆዬቱ ነው።

ጣልያን ይዞታዋን ለማስፋትና በተለይም በአድዋ ጦር ሜዳ የደረሰባትን ውርደት ለመበቀል ከአርባ ዓመት ዝግጅት በኋላ ጦሯን ስታንቀሳቅስ በአጼ ሃይለሥላሴ የሚመራው የኢትዮጵያም መንግሥት ገና ለማደግ ፤ካለፈውም ስብራትና ኋላ ቀርነት ለመላቀቅ በሚድህበት ጊዜ ዳግም ወረራ ተከፈተበት።ጊዜው በፈቀደለት አቅሙ ጦሩን ከቶ በማይጨው ጦር ሜዳ ላይ ተፋለመ።ግን ጊዜውና ዝግጅቱ፣የዓለምም ወራሪ ሃይሎች ባላቸው የህብረት ሰንሰለት ምክንያት ድሉ የወራሪው ጣልያን ሆነና ከሰሜን አልፎ መሃል አገር እዬሰነጠቀና እዬተቆጣጠረ ያገሪቱን መናገሻ ከተማ አዲስ አበባን ተቆጣጠረ።ከዚያም አልፎ ያገሪቱን ክፍላተሃገር በመዳፉ ስር አስገባ።በዚህ ጊዜ ከጳጳፓሳት፣ከባላት እስከ

ተራው ድረስ ለጠላት አዳሪው ተበራከተ።ይህም ሆኖ ግን አሻፈረኝ ያለው አገር ወዳድ እጁን አልሰጠም እስከሚችለው ድረስ ዱር ቤቴ ብሎ በነበዝ አለቆች እዬተመራ ጠላትን በሽምቅ ውጊያ ይፋለመው ጀመር።

በአጭር ጊዜ ውስጥ ዘመናዊ መከላከያ ሃይል ለመመስረት ሰልጥኖ የነበረው ጥቂት ወታደር ጥቁር አንበሳ በሚል ስያሜ ወታደራዊ ጥቃት ማድረሱን ተያያዘው።በዚህ ጊዜ ነበር በተለይም የእዝ ማእከሉን በኢሉባቦር ጎሬ ያደረገው በራስ እምሩ ሃይለሥላሴ የሚመራው የኢትዮጵያ መንግሥት የጦር ሃይል በምዕራብና ደቡብ ኢትዮጵያ የነጻነት ትግሉን አፋፍሞት የነበረው።የጣልያን የፕሮፓጋናዳና የአዬር ጥቃትም በዚሁ አካባቢ የበረታ ሆነ። የከባቢው የኦሮሞ ባላባቶችና ለጠላት ያደሩ ባንዳዎች ፕሮፓጋንዳውን ተቀብለው በራሳቸው አገርና የነጻነት ታጋይ ላይ የጥቃት እጃቸውን ዘረጉ። የከባቢው ባላባቶችና ያደሩ ባንዳዎች ሕዝቡን ጣልያን እኛን ነጻ ለማውጣት የመጣ ነው በማለት ቀስቅሰው እጁን በእጁ እንዲቆርጥ አደረጉት።አርበኞችን በመከበብና በመነጠል፣ስንቅና ትጥቅ ነፍጎና ቀምቶ የገደለውን ገሎ የቀረውን በጠላት እንዲማረክ አደረጉት።እራስ እምሩና የቀሩት መሪዎችም ተማርከው ለግዞት ወደ ጣሊያን አገር ተወሰዱ።ምንም እንኳን ለጊዜው የአርበኞቹ ትግል ቢዳከምም በሌላው ቦታ በተለይም በአማራው መኖሪያ በጎጃም፣በሸዋ፣በወሎና ጎንደር ውስጥ የአርበኞቹ ትግል ተፋፍሞ እስከድል ድረስ ዘለቀ። ከድል በኋላ ባንዳና ከሃዲው በይቅርታ መታለፍ ብቻም ሳይሆን ለሹመትና ለሽልማት የመጀመሪያው ሆነ።አርበኛውም ለሹመትና ሽልማት ሳይሆን ለአገሩ ክብርና ነጻነት በመታገሉ ቅር ሳይለው በድል አድራጊነቱ ብቻ ተደስቶና እረክቶ ፣ትዝብቱን

አገሬ ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ ፣

የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ።

ሲል ገልጾታል።የካዱትንና በባንዳነት ያስጠቁትን ስራቸውን ባይዘነጋም ለአንድ አገር ሲል በይቅርታ ልቡን ከፍቶ በጋብቻና በአበልጅነት አቅፎ ለመኖር ቻለ።

ከጣሊያኖች በኋላ ለአስር ዓመታት በኢትዮጵያ የፖለቲካና መንግሥታዊ አሠራር ውስጥ ጣልቃ የገባችው እንግሊዝ ከጣልያን ያልተለዬ የተንኮልና አገር የመበታተን ሥራዋን ሠራች። የሰሜኑን ኤርትራን በሞግዚትነት ይዛ በቆዬችበት ጊዜ መሰሪ ሥራዋን ከመሥራት አልቦዘነችም።ያንን ልቡ የሸፈተ ተላላ ሕዝብ በደካማ ጎኑ እዬገባች በገዛ አገሩ ላይ እንዲሸፍት አደረገችው።በሃይማኖትና በፖለቲካ እረድፍ የሚንቀሳቀስ የኤርትራ ነጻ አውጭ አማጽያን ችግኝ ተከለች።የኢትዮጵያን መሬት እዬቆረሰች በቅኝ ግዛትነት ለያዘቻቸው ጎረቤት አገራት በተለይም ለሱዳንና ኬንያ አስረከበች።አሁን በአልፋሽካና በሌሎቹ የድንበር አካባቢዎች የተነሳው ግብግብ የዚያ ውጤት ነው።ያንን ተከትሎ ፈረንሳዮቹም የገቡትን ስምምነት ጥሰው ጅቡቲን አንለቅም ካሉ በኋላ ሁኔታው አስገድዷቸው ሲለቁ ከኢትዮጵያ የተነጠለች ነጻ አገር አደረጓት። አሁን ላይ ሁሉም

ተግደርዳሪ የውጭ ሃይል በጎሪጥ የሚተያይባትና የመሳሪያ ማራገፊያ በራሷ መቆም የማትችል ሚጢጢ አገር ሆናለች።ኢትዮጵያም በራሷ ወደብ ለነበረ ቢሊዮን ዶላር የምትከፍል ጥገኛ አገር ሆነች።

እንገሊዞች ኢትዮጵያን ለማዳከምና ለመበታተን ካቀዱት ሴራ ውስጥ ሰሜኑን ክፍል ትግራይ ትግርኛ የሚል ስያሜ ያለው አገርና መንግሥት እንዲቋቋም፣የምዕራብ ኤርትራን ክፍል ከሱዳን ጋር ለማቀላቀል፣የምዕራብና ደቡብ ኢትዮጵያን ኦሮሚያ የሚል  ነጻ አገር እንዲፈጠር የታቀደ ሴራ ነበር።ይህ ህሳቤ በተወላጁ አይምሮ ውስጥ ሰርጾ ከዓመታት በኋላ  ገሃድሆነ።

በጣልያኖችና በእንግሊዞች የተቀመረው ኢትዮጵያን የመበታተኑ ሴራ ኤርትራን፣ ትግራይንና ኦሮሞን ገንጥሎ አገር ለማድረግ በሚፈልጉ ሃይሎችና በውጭ ተባባሪዎቻቸው የተቀሰቀሰው ጦርነት እስከአሁን ድረስ አገራችንን ለቀውስና ሕዝቧንም ለመከራ ዳርጎ ቀጥሏል።ኤርትራ እራሷን የቻለች አገር ብቻም ሳትሆን የኢትዮጵያ ታሪካዊ ወደቦችን ነጥቃ ኢትዮጵያን ወደብ አልባ ያደረገች አገር ሆነች።የትግራይ ተገንጣዮች ለ27 ዓመት ያገሪቱን ስልጣን ጨብጠው ያሻቸውን ሲያደርጉ ከቆዩ በኋላ በሕዝቡ ትግል ተወግደው መቀሌ ገብተው መሽጉ።ኢጋጣሚውን የኦሮሙማው ተረኛ ቡድን ተጠቅሞ ስልጣኑን ተቆጣጠረው።

ከቀድሞ ኢጋሩና አለቃው ከነበረው የወያኔ ቡድን ጋር የሥልጣንና የጥቅም ግጭት ተነስቶ ሲካረርና ወደ ጦርነት ሲገባ  ቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ የአገሩን አንድነት ያስጠበቀ መስሎት ከኦሮሙማው ጎን ተሰልፎ ተዋጋ።ድል ለማድረግም በቃ። በማግስቱ ግን የኦሮሙማው ቡድን ውለታውን ዘንግቶ ሥልጣኑን ባስጠበቀለት ሕዝብ በተለይም በአማራው ላይ ጦሩን መዘዘ። ላለፉት አምስት ዓመታት በምድር ላይ ተፈጽሞ ያልታዬ ጭካኔ እዬፈጸመ የጣልያንና የእንግሊዞቹን እቅድ ለማስፈጸም ኢትዮጵያን ከመሃል ሆኖ መበታተኑን ተያያዘው።ኢትዮጵያን ኦሮሞ ማድረግ አለያም መበታተንና በፍርስራሿ ላይ ኦሮሚያ የምትባል በታሪክ ያልነበረች በትርክት የተሳለች አገር ለመፍጠር ባንኩንም ታንኩንም ዘርፎ የራሱን ሃይል አካበተ።በተለያዩ የጥፋት ሃይሎች ስም አገርወዳዱን በተለይም የአማራውን ተወላጅ ከኢትዮጵያ መሬት ብቻም ሳይሆን ከምድር ገጽ ለማጥፋት ያለ የሌለ ሃይሉን አሰልፎ ጥቃቱን ቀጠለበት።በቃላት ደንዝዞ ለውጥ መጣ ብሎ በተቀበለው የዋህ ሕዝብ ላይ ከያቅጣጫው የጥፋት ክንዳቸውን አሳረፉበት።

ኢትዮጵያን ለማጥፋት ሲመቻቸው አንድ ላይ ፣ጥቅም ሲለያቸው ሲዋጉ የኖሩት የወያኔና የኦነግ ቡድኖች ከሚሊዮን ሕዝብ በላይ በጦርነት ማግደው ካስጨረሱ በኋላ  ተሳስመው የጋራ ጠላታችን ነው በሚሉት በኢትዮጵያዊነትና በአማራው ላይ ጥምር ክንዳቸውን ለማንሳት ተስማሙበት።በአደባባይም እራሳቸውን የሰላም ጠበቃ አድርገው ተሞካሹበት፣ ተሸላለሙበት፣አማራውን ለሰላም ያልቆመ፣ ቁሞቀር፣ነፍጠኛና አሃዳዊ እያሉ ወነጀሉት፣ ሳቁበት ዘበቱበት።ለዚህ ውርደትና ውድቀት የዳረጉት በአማራው ስም  ብአዴን የሚል

ጭንብል አጥልቀው፣ከአናቱ ላይ የተቀመጡት ፣ በባንዳነት የሚያገለግሉ አማራዎቹ ናቸው።

በዚህ ሂደት ውስጥ የምዕራባውያን አገሮች በተለይም የአሜሪካና የአረቦች ጥምረት ተሳትፎ መኖሩ ገሃድ የወጣ ሃቅ ነው።ለወያኔ ሽንጣቸውን ገትረው መከራከራቸው፣የጦር መሣሪያ ማቀበላቸውና የዲፕሎማሲ ድጋፍ ከማድረጋቸው በዘለለም የአማራውን መኖሪያ አጽመ እርስቱን ነጥቆ የትግራይ ነው ብሎ እውቅና መስጠቱ የግንጠላ ሂደቱን የማጠናከር ሴራ መሆኑን የማይረዳ ይኖራል አንልም።በኦነግም በኩል እንዲሁ ድጋፋቸውን እዬቸሩት ነው።ለስሙ ሰብአዊ መብት ቆመናል ቢሉም የሰው ልጅ ከማህጸን እዬተጎተተ ሲረገጥ፣ ህጻን ሽማግሌ አሮጊት ሴት ወንድ ሳይባል በገጀራና በቆንጨራ አንገቱን ሲቀላ፣ስጋው ሲቆራረጥ፣መቃብር ተነፍጎት ያውሬ ቀለብ ሲሆን እያዩና እዬሰሙ አንዲት ቃል ትንፍሽ አለማለቱን መርጠዋል።ምክንያቱም የሚገደለው፣የሚጨፈጨፈው፣የሚፈናቀለው አገር ወዳዱና ለባእዳኑ አገዛዝ የማይመች ዜጋ ፣አማራ በመሆኑ ነው።ለኦነግ የትጥቅና ስንቅ ፣ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ድጋፍ ከሚያደርጉት የምዕራብ አገሮች መካከል በዋናነት ጀርመን፣ስዊድን፣ እንግሊዝ፣ አይርላንድ፣ኖርወይና ኔዘርላንድስ ይገኙበታል።ለወያኔዎቹም እንዲሁ ጣልያንን ጨምሮ ከሚረዱት አገሮች መሃል የተጠቀሱት አገሮች ዋናዎቹ ናቸው። በተጨማሪ የግብጽ፣የሱዳን፣የአረብ አገሮችም በበኩላቸው ለሚፈልጉት ዓላማ ይረዳናል ያሉትን ከመደገፍ አልቦዘኑም።አጋርና ደጋፊ ያጣው ለኢትዮጵያ አንድነትና ነጻነት ምሰሶ ሆኖ የኖረውና እስከአሁንም ድረስ የቆዬው የአማራው ሕዝብ ነው።የውጨም የውስጡም እንደማርያም ጠላት የሚረባረብበት በዚሁ አገር ወዳድ ሕዝብ ላይ ነው።

ይህንን ዓለም አቀፋዊ ሴራ ያልተገነዘበው ሌላው ማህበለሰብ ተወላጅ ኢትዮጵያዊ የኦነጋውያኑና የወያኔዎቹ ሴራ ለመብትና ለእኩልነቱ የሚደረግ ትግል መስሎት የወያኔና የኦነግን አጥፊ ሃይል ከመዋጋት ይልቅ በልመናና በታዛዥነት መብቱን የሚያስከብር መስሎት ሲጃጃል ይታያል።መሬቱን እዬሸረሸሩ ሲጠቀልሉትም አልገባውም።በውስጥ ባንዳዎቹ ጫጫታ ተወናብዶ እራሱን ለጥፋት አጋልጦ ተቀምጧል። የጉራጌ ማህበረሰብ እምቢ ለማለት ሲግደረደርም በወታደር ሃይል ሲወረርና በጥይት ሲደበደብ እያዬ ነግ በእኔ የሚል ስጋት አላደረበትም፤በአጠቃላይ ወደ ቄራ የሚነዳ ከብት ሆኗል።ይህ ሁኔታ ካልተቀዬረ ሁሉም አገረቢስ የሚሆንበት ዕድሉ ትልቅ ነው።መከራው በአማራው ብቻ አይቀርም፣የሁሉም እጣ ፈንታ ይሆናል።ከዚያ ለመዳን የሚቻለው ሃይሉን አስተባብሮ በአንድ አገር ልጅነት፣በኢትዮጵያዊነት መታገል ሲችል ብቻ ነው።

ሰላም ትርጉምና ዋጋ ቢስ መሆኗንም በሰሞኑ ታዝበናል።ከሚሊዮን ሕዝብ በላይ ላለቁበት ጦርነት ተጠያቂ የሆኑት ወያኔና ኦነግ ለጊዜውም ቢሆን በመካከላቸው ያለውን ሽኩቻ አሶግደው በአማራው ላይ ሃይላቸውን አስተባብረው ለመነሳት የተቃቀፉበትና ቃል ኪዳን የገቡበትን ድራማ በአደባባይ ታዝበናል።የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳ እንዲሉ ወያኔ ለጊዜው አንገቱን ቢደፋም ቂሙን እረሳ፣የመገንጠል ምኞቱን ዘነጋ ማለት አይደለም።

የስልት ለውጥ በማድረግ።በጦርነት ያላገኘውን ለመገንጠል ቅድመ ሁኔታ የሆነውን የወልቃይትንና የራያን መሬት በአነግ ትከሻ ላገኝ እችላለሁ ከሚል ጉጉት የተነሳ እንጂ።

በዚሁ ትርጉመቢስ የሰላም ድራማ አማራውን ሲገል፣ሲጨፈጭፍና ሲያፈናቅል በጫካ የኖረው የአነጉ ጦር ቤተመንግሥት ካለው የአነግ የፖለቲካ ክንፍ ጋር ተባብሮ መሥራቱ እዬታወቀ ተቀናቃኝ በማስመሰል አሸባሪ ብሎ በፓርላማ ካስፈረጀ በኋላ ከተጠያቂነት ለማምለጥ ለእርቅ ድርድር በሚል ሽፋን ሕጋዊነት እንዲኖረው ለማድረግ በታንዛንያ ስምምነት ለመፈራረም መወሰኑን ይፋ አድርጎ ተንቀሳቅሷል።በዚህም ላሙኛችሁ ጨዋታ ከበሮ ደላቂዎችና የውሉ አባት የሆኑት የአውሮፓ አገሮችና አሜሪካኖቹ ናቸው።

የአገር ቤቱን ቀውስ ተከትሎ በሱዳን የተከሰተው የሁለት ጀነራሎች የስልጣን ሽኩቻ ያመጣው ቀውስና ጦርነት የኢትዮጵያን የፖለቲካ ሃይሎች  ከሁለት ጎራ መክፈሉን ታዝበናል።መንግሥት ተብዬው በሁለቱም በኩል ለማጭበርበር የሚከተለው ስልት የትም ባያደርሰውም ከአሜሪካኖቹ ብብት ውስጥ ላለመውጣት፣የሚጠብቀውንም የገንዘብ እርዳታና ብድር ላለማጣት ሲል የአልቡርሃንን ጎራ መደገፉን የመረጠ ይመስላል። አሜሪካኖች ምንጊዜም ከአሸናፊው ጋር የመሆን መገለባበጥ ባህላቸው ስለሆነ የዛሬው አቋማቸው ለነገው ዋስትና አይሆንም።ቋሚ ወዳጅና ቋሚ ጠላት የለም የሚሉት መመሪያቸውም የዚሁ መገለባበጫ ገመዳቸው ነው።

ኤርትራ ከአሜሪካኖቹ ጋር ባላት የቆዬ ልዩነትና ከሩስያ ጋር ባላት ግንኙነት ሳቢያ የአልቡርሃንን መንግሥት ተቃውማ በተቋሚ በሙሃመድ ሃምዳድ ጋደሎ ጎራ መሰለፉን መርጣለች።ጦሯንም በኢትዮጵያና በሱዳን ድንበር ላይ አጠናከራለች።የከሰላ አካባቢም የኔነው ማለትም ጀምራለች።ጦርነቱ ከቀጠለ ከባቢውን የሚበክል የቀጠና ውጊያ የመሆኑ ዕድሉ ከፍተኛ ነው።አቅጣጫውም ያንኑ ያመላክታል።ይህ ከሆነ ደግሞ ለኢትዮጵያ በአንገት ላይ ጆሮ ደግፍ ወይም በቡሃ ላይ ቆረቆር ይሆንባታል ማለት ነው።

የሱዳንን ቀውስ ተከትሎ በኢትዮጵያኑ በተለይም በአማራው የፖለቲካና የታጠቁ አካላት(ፋኖ) በኩል የራሳቸውን አቋም ይዘዋል፣ድጋፋቸው ለአማጽያኑ እንደሚሆን ምልክቶች ይታያሉ።የሚሰጡት ምክንያት በአልቡርሃን መንግሥት ወታደር የተነጠቅነውን መሬት አሁን ስለያዘን ተቃዋሚው ጄነራል ሥልጣን ቢይዝ ለመንጠቅ አይሞክርም የሚል ምክንያት በማቅረብ ነው።ለጊዜው እስኪጠናከር ድረስ ሊሆን ይችላል፤መዘንጋት የሌለበት ማንም ቢሆን የሱድንን በትረመንግሥት የጨበጨ ሃይል ያገሩን ጥቅም አሳልፎ አይሰጥም።ጊዜ ሲያመቸውና ሲረጋጋ ያልያዘውን ለመያዝ ይነሳል።እንደውም በሕዝቡ ተቀባይነትን ለማግኘት የመጀመሪያ እርምጃው ለአገር ዳር ድንበር መቆሙን ማሳዬት ነው።አገር ጠል የሆነ የመከላከያ ተቋም ባለቤት የሆነችውን ኢትዮጵያን መውረርና የአልፋሽካን ለም መሬትን ማስመለስና መቆጣጠር ቀላሉ እርምጃ ነው።ለኢትዮጵያ የሚበጃት የራሷን ጥቅምና ልዑላዊነት የሚያስጠብቅ መንግሥትና ሃይል እንዲኖራት ማድረግ ነው።ከማይሆን ጋር ማበርና ጊዜያዊ መቀራረብ ዘላቂ ሰላም አይፈጥርም።

ለኤርትራም ሆነ ለኢትዮጵያ የሚበጀው ነገር ከሱዳኖች ጀነራሎች ጋር መፋተጉና መተሻሸቱ ሳይሆን ለጋራ ጥቅማቸው አብረው ቢቆሙ የተሻለ ነው።የኤርትራና ቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት አብሮ የኖረ፣የተዋለደ፣በታሪክ፣በስነ ልቦና፣በቋንቋና ፊደል፣በሃይማኖት፣በኤኮኖሚ፣በመሬት አቀማመጥ ወዘተ በብዙ መስተጋብሮች የተሳሰረ ስለሆነ እጣ ፈንታው አንድ አይነት ነው።የምዕራባውያኑ  በተለይም የአሜሪካኖች ሴራ ለሁለቱም ሕዝቦች አንድ አይነት አደጋ አለው።ሌላው ቢቀር በጋራ የሚቆሙበት የፌዴራል ትስስር ቢኖራቸው ለእድገታቸው፣ለሰላማቸው የበለጠ ዋስትና ይኖረዋል።ይህ ካልሆነ ግን ኢትዮጵያ ውስጥ የተጫረው እሳት ለኤርትራም ይተርፋል።የጎሳና የሃይማኖት ግጭት ሁለቱንም የሚያሰጋ የተቀበረ ቦምብ ነው።ይህንን ቦምብ ለማፈንዳት ምዕራባውያንና አሜሪካኖች ጊዜ እዬጠበቁ መሆናቸውን ልብ ማለትና ቀድሞ መዘጋጀት ከሚመጣው አደጋ ያድናል።ኢትዮጵያን  ለመበታተን የደፈሩና የተነሱ ለኤርትራ ልዩ ፍቅር ይኖራቸዋል ተብሎ አይታሰብም።በዬትኛውም ቦታ የነሱ ቡችላ ካልሆነ በቀር አገር ወዳድ መንግሥት እንዲኖር አይሹም።በረጅም ገመድ የታሰረች ዶሮ ነጻ ነች ማለት አይደለም።ጊዜው ሲደርስ ባሳሪዋ ትታረዳለች።

ማጠቃለያ

ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ ጠላቶቿ እዬተስማሙና እዬተሰባሰቡ በመሄድ ላይ ናቸው።ዙሪያ ገጠሙ፣ዳርድንበሯ በእሳት ይጋያል።የገና ዳቦ ይመስል ከላይም ከታችም ትጠበሳለች። ከዚያ ሰደድ ለመውጣት ያላት አማራጭ አንድ ብቻ ነው።ሕዝቧ በአንድነት ተነስቶ አገር አጥፊውን የኦሮሙማና የወያኔ ሃይል ማሶገድ ብቻ ነው።የውስጥና የውጭ ጠላቶቿን ማወቅና  ሳይንበረከክ እንደ አገር ነጻነቷንና አንድነቷን እንዲሁም ልዑላዊነቷን የሚያስከብር መንግሥት መመስረት ብቻ ነው፣ያንን ሃይል የሚሰበስብ አንድ ብሔራዊ (አገር አቀፍ)ግንባር መቋቋም ነገ የማይሉት አጣዳፊ ተግባር ነው።

በውስጥ ያለው ታጋይ ህይወቱን መገበሩ ሳያንሰው ፣ትግሉ ውጤታማ እንዲሆን ከተፈለገ አገር ወዳዱን ያቀፈ፣ከሁሉም የተውጣጣ የፖለቲካ ፣የወታደራዊና የግንኙነት ክንፍ ያለው ግንባር መፍጠር ይኖርበታል።በውጭ አገር የሚኖረውም አገር ወዳድ እንዲሁ በመካከሉ ያለውን ትርጉም አልባ ጭቅጭቅና ልዩነት አሶግዶ ለአገር አድኑ ትግል የሚታገለውን የተበታተነ ሃይል የጋራ ግንባር እንዲፈጥር መጠዬቅ ይኖርበታል። እሱም የሚያደርገውን ድጋፍ የሚረከብና ተጠያቂነት ያለው አካል ሊፈጥር ይገባል። በውስጡ የሚርመሰመሱ አስመሳዮችን፣ባንዳዎችንና ጥቅመኞችን ማጽዳቱ ለትግሉ ዋስትና ነው።ሰርጎ ገቦችን ማሶገድም እንዲሁ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።በሃይማኖት ተቋማት፣በመረዳጃ፣በብዙሃኑ ድርጅቶች፣በማህበራት ውስጥ የሚርመሰመሱትን  የስርዓቱን ደጋፊዎች መነጠል አንዱ የትግሉ ምዕራፍ መሆን አለበት።

የብአዴኑ የኦነግ ተላላኪ የነበረው የግርማ የሸጥላን መገደል በተመለከተ ምንም እንኳን ግልጽ የሆነ ማስረጃ ባይኖርም ካለፉት ግድያዎች ስንነሳ የአብይ አህመድ /የኦህዴድ ሴራ

ውጤት ለመሆኑ ብዙ ሃሳቦች እዬተሰነዘሩ ነው።እኛም ሃሳቦቹን እንጋራለን።አብይ አህመድ ገና ከጅምሩ በመጽሓፉም እንደገለጸው ሰዎችን የሚፈልጉትን እያሳዬህ ወደ ምትፈልገው ውሰዳቸው፤ከዚያም በሬ ሆይ ሳሩን አይተህ ገደሉን የሚለውን ተርትባቸው ብሏል።አዎ የብአዴንን አጋሰሶች በሹመትና በሽልማት አደንዝዞ በራሳቸው ሕዝብ ላይ ግፍ እንዲፈጽሙ አድርጓቸዋል፣ያንንም አድርገው አይምራቸውም፤ከሕዝብ ከነጠላቸውና ላገልግሎት የማይውሉ ምናምንቴ ሲሆኑ በጠራራ ይዘርራቸዋል፤በሴራ ያሶግዳቸዋል። መቼም ባይሞቱም ከርሰመቃብር ያልገቡ የቁም ሙቶች ናቸው።የአሁኑን አሟሟት ለዬት የሚያደርገው የአማራው ማህበረሰብ የግፉ ዋንጫ ሞልቶ ሲፈስ ለመብቱና ለአገሩ አንድነት ለመታገል ቆርጦ በተነሳበት ሰዓት መሆኑ ነው።ይህንንም ግድያ አማራውን በወንጀለኛነት ፈርጆ በአገር ሃብት ያዘጋጀውን የአነግ ጦሩን ለማዝመትና ሰጥ ለጥ ለማድረግ ያዘጋጀው ወጥመድ ነው።በአንድ ጠጠር ሁለት ወፍ እንዲሉ ፣የማይረባውን ምናምንቴ ማሶገድና በእሱ ጀርባ ተቃዋሚውን ሕዝብ ወንጅሎ ለማንበርከክ የክተት አዋጅ ማወጅ።ይዋል ይደር እንጂ አነጋውያኑ አብይ አህመድን ጨምሮ የወጥመዱ ሲሳይ የሚሆኑበት ዕድሉ ሰፊ ነው።የሚወስነው ግን የሕዝቡ ብርታትና በአንድነት ቆሞ መታገሉ ነው።ግድያው በግርማ የሸጥላ ብቻ አይቆምም ሌሎቹም ከሕዝብ የራቁና አንቅሮ የተፋቸው፣የአገልግሎት ዘመናቸውን የጨረሱ ወደመታረጃቸው የሚነዱ አጋሰሶች ናቸው።

ቢሞቱ ነፍሳችሁን ይማረው ሳይሆን በሰማይ ቤት የሥራችሁን ይስጣችሁ እንላለን።

ድል የተደራጀ ህዝብ የትግል ውጤት ነው!የተደራጀን በማፍረስና በማዳከም ሌላ ድርጅት መፍጠርና እንደአሜባ መራባት የጠላትን ተልእኮ በአዙሪት መንገድ ማስፈጸም ይሆናል።ስለሆነም በዬቦታው ተለያይቶ ስብሰባ ከመጥራት ይልቅ ቀደም ብሎ በተፈጠረና የትግል ልምድ ባለው ውስጥ መካተትና ድክመቶች ቢኖሩበት ማስተካከል የሃቀኞች ተግባር ነው።በተለይም የአማራውን ህልውና ለማስከበር ቀደም ብሎ ከተደራጀው የአማራ ድርጅት ጋር መቆም አማራጭ የሌለው ምርጫ ነው።ከዚያ ውጭ የተለዬ ተልእኮ ያለው ያስመስላል።ሊሆንም ይችላል።ለአንድ አማራ አንድ ድርጅት የምንለውም ለዚያ ነው።

አንድ አገር!አንድ ሕዝብ! አንድ ሕዝባዊ ግንባር!!